**የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።» 2ጢሞ. 3÷16-17**




**«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤
ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።»
መዝ. 118(119)÷130**

**Global Good News Literature**
**የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት**
**P.O.BOX 451336**
**Los Angeles, CA 90045**
email: info@globalgoodnews.org
**Copyright © 2008**



## ማውጫ

**ክፍል ፩**


| | ገጽ |
|---|---|
| ትምህርት አራት፡- እምነት ........ | 5 |
| እምነታችን በተለያዩ ነገሮች ላይ ሊሆን ይችላል ........ | 5 |
| ፩. እምነት (እግዚአብሔርን ማመን) ስንል ምን ማለታችን ነው? | 5 |
| ፪. እምነት በክርስትና ሕይወታችን ሊኖረው የሚገባው ስፍራ | 6 |
| ፫. የእምነት ደረጃዎች ........ | 8 |
| ፬. እምነት ከየት ይመጣል? ........ | 9 |
| ፭. እምነታችን እንዴት ያድጋል? ........ | 10 |
| ፮. እምነት እንዴት ይገለጣል? ........ | 11 |
| ፯. የእምነት ጠላቶች ........ | 11 |
| ትምህርት አራት፡- እምነት - ጥያቄዎች ........ | 16 |

## የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት
## የመላላክ ትምህርት

የዚህ የመላላክ ትምህርት ዋና ዐላማ በጌታ ዐዲስ ለሆኑ፣ እንዲሁም በጌታ ከሆኑ ቈየት ቢሉም፣ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የበለጠ ለማጠናከር ለሚፈልጉ ወንድሞችና እኅቶች መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ለማስተማርና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ መርዳት ነው። «ፈረስን ወደ ውሃ ታመጣዋለህ እንጂ እንዲጠጣ አታስገድደውም» እንደሚባለው ሁሉ፣ እነዚህ ትምህርቶች ተማሪው በትጋት ካልተከታተላቸውና በውስጣቸው ያሉትንም ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እያመሳከረ በሚገባ ካላጠና፣ እንዲሁ በአንድ ጊዜ ንባብ ብቻ የሚፈለገውን ውጤት ያስገኛሉ ማለት አዳጋች ነው። ስለዚህ ይህንን ትምህርት የምትከታተሉትን ሁሉ፣ እያንዳንዱን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አውጥታችሁ ጥቅሶቹን በማመሳከር በትጋት፣ እንድታጠኑት እናበረታታለን።

እነዚህን ትምህርቶች በግልም ሆነ በኅብረት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ መጠቀም ይቻላል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጀማሪዎችን የማስተማር ኀላፊነት ያለበት ሰውም ሌሎችን ለማስተማር ሊጠቀምባቸው ይችላል። ትምህርቶቹን በእኛ በኩል በግል ለመከታተል የምትፈልጉ ግን በመጀመሪያ መመዝገብና የመታወቂያ ቍጥር መቀበል ይኖርባችኋል። ከዚያም ከእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ ላሉት ጥያቄዎች በቂ መልስ በመላክ የመላላኩን ትምህርት መቀጠል ትችላላችሁ።

የመላላክ ትምህርቱ፣ ዐሥራ ሁለት መሠረታዊ የሆኑ ትምህርቶችን ያካተተ ሲሆን፣ አራት አራቱን ከፋፍለን በሦስት ክፍሎች አቅርበናቸዋል። አርእስቱ፣ ለአንድ ክርስቲያን ያስፈልጋሉ ብለን ያመንባቸው አርእስት ናቸው። ትምህርቶቹን በጥሞናና በረጋ መንፈስ አጥንታችሁ ከትምህርቱ ጋር የተገናዘበ በቂ መልስ እንጂ በችኰላ የቸልተኝነት ወይም ከትምህርቱ ጋር የማይዛመድ መልስ እንዳትሰጡ ልናሳስብ እንወዳለን።

ትምህርቶቹን በደንብ አጥንታችሁ የጥያቄዎቹን መልስ፣ በየክፍሉ ያሉትን አራት አራት ትምህርቶች በየተራ፣ ወይም የዐሥራ ሁለቱንም ትምህርቶች በአንድነት ስትልኩልን፣ መልሳችሁን አይተን ይህንን የመላላክ ትምህርት እንደ ጨረሳችሁ የሚገልጽ የምስክር ወረቀትና ትራንስክሪፕት እንልክላችኋለን።





# ክፍል ፩



«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤
ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።»
መዝ. 118(119)፥130

## ትምህርት አራት፡- እምነት

እምነት በአንድ ነገር፣ በአንድ ግለሰብ ወይም በራስ ላይ መደገፍና ተስፋ ማድረግን ያመለክታል።

### እምነታችን በተለያዩ ነገሮች ላይ ሊሆን ይችላል

1. **እምነታችን በራሳችን ላይ መሆን የለበትም፤**

«ሙታንን በሚያስነሣ በእግዚአብሔር እንጂ በራሳችን እንዳንታመን፤ » (2ቆሮ. 1÷9)

«እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን... ነን።» (ፊል. 3÷3)

2. **እምነታችን በሌላ ሰው ወይም በሁኔታዎች ላይ መሆን የለበትም፤**

ኤር. 17÷5-6 ላይ «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በሰው የሚታመን ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ፣ ልቡም ከእግዚአብሔር የሚመለስ ሰው ርጉም ነው። በምድረ በዳ እንዳለ ቍጥቋጦ ይሆናል። መልካምም በመጣ ጊዜ አያይም፤ ሰውም በሌለበት ጨው ባለበት ምድረ በዳ በደረቅ ሥፍራ ይቀመጣል» ይላል።

ኤር 9÷23 ላይም፣ «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ ጠቢብ በጥበቡ አይምካ፤ ኃያልም በኃይሉ፤ አይመካ፤ ባለጠጋም በብልጥግናው አይመካ....» የሚለውን እናነባለን።

3. **እምነታችን በእግዚአብሔር ላይ መሆን አለበት፤**

«በእግዚአብሔር የታመነ እምነቱም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ቡሩክ ነው። በውኃ አጠገብ እንደ ተተከለ፤ በወንዝም ዳር ሥሩን እንደሚዘረጋ፤ ሙቀትም ሲመጣ እንደማይፈራ፣ ቅጠሉም እንደሚለመልም፣ በድርቅ ዓመትም እንደማይሠጋ፤ ፍሬውንም እንደማያቋርጥ ዛፍ ይሆናል።» (ኤር. 17÷7-8)
«ነገር ግን የሚመካው ምሕረትንና ፍርድን ጽድቅንም በምድር ላይ የማደርግ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን በማወቁና በማስተዋሉ ይመካ፤ ደስ የሚያሰኙኝ እነዚህ ናቸውና ይላል እግዚአብሔር።» (ኤር. 9÷24)

በዚህ ትምህርት ትኩረት የምሰጠው በእግዚአብሔር ላይ ሊኖረን ለሚገባ እምነት ነው።

### ፩. እምነት (እግዚአብሔርን ማመን) ስንል ምን ማለታችን ነው?

እምነት፤ እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል መፈጸም ይቻለዋል ማለት ነው።





«እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፣ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።» (ዕብ. 11÷1)

ሮሜ 4÷18-22 (በዐዲሱ ትርጕም)፣ «አብርሃም ያመነውና ተስፋ ያደረገው ምንም ተስፋ ባልነበረበት ጊዜ ነው፤ ስለዚህ ዘርህ ይህን ያህል ይበዛል ተብሎ በተጻፈው መሠረት የብዙ ሕዝብ አባት ሆነ። ዕድሜው መቶ ዓመት ያህል ስለ ነበረ፣ በሥጋው መድከም ምክንያት መውለድ እንደማይችልና ሣራም መኻንና ያረጀች በመሆንዋ መውለድ እንደማትችል ቢያውቅም በእምነቱ ደካማ አልሆነም። በእምነቱ ብርቱ ሆኖ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ የሚፈጽም መሆኑን ስለ ተረዳ ነው። እንግዲህ አብርሃም እምነቱ ጽድቅ ሆኖ የተቈጠረለት ስለዚህ ነው። ነገር ግን «ጽድቅ ሆኖ የተቈጠረለት» የሚለው ቃል የተጻፈው ለአብርሃም ብቻ ሳይሆን ለእኛም ጭምር ነው። ጌታችን ኢየሱስን ከሞት ባስነሣው አምላክ ለምናምን ለእኛም እምነታችን ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርልናል» ይላል።

ከእነዚህ ጥቅሶች የምንረዳው፣ ከእምነት በፊት እግዚአብሔር የሰጠ ው የተስፋ ቃል መኖር እንዳለበት ነው። እምነት ሊቆም የሚችለው በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ላይ ብቻ ነው። የራሳችንን ምኞትና ሕልም ከልባችን አመንጭተን ይህንን ነገር እግዚአብሔር እንደሚያደርግልኝ አምናለሁ ብንል፣ ያ ነገር እግዚአብሔር ከሰጠው የተስፋ ቃል ውጪ ከሆነ አይሆንልንም። በዐጭሩ ከእምነት በፊት እግዚአብሔር የተናገረን የተስፋ ቃል ሊኖረን ይገባል።

ተስፋ ያለው ሰው «ይሆናል» ይላል፤ እምነት ያለው ሰው ደግሞ «ሆኖአል» ይላል። «እምነት ተስፋ የምናደርገውን ነገር የሚያስረግጥ» ነውና።
«የለመናችሁትን ሁሉ እንዳገኛችሁ እመኑ ይሆንላችሁማል።» (ማር. 11÷24)

እምነት በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ላይ ተደግፎ «የለመንሁት ነገር ሆኖልኛል» ይላል።

አብርሃም ያደረገው ይህንን ነበረ፤ «እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ ባለማመን ከቶ አልተጠራጠረም። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ የሚፈጽም መሆኑን ስለ ተረዳ ነው።» (ሮሜ 4÷20-21) እምነት ሁልጊዜ እግዚአብሔር የተሰጠውን የተስፋ ቃል ይፈጽማል ብሎ አጥብቆ ይረዳል።

### ፪. እምነት በክርስትና ሕይወታችን ሊኖረው የሚገባው ስፍራ

1. ያለ እምነት እግዚአብሔርን ማስደሰት አይቻልም። (ዕብ. 11÷6)

ደካማ እምነት ያለው ክርስቲያን እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይችልም። እግዚአብሔር አይወደውም ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ሁሉንም በአምላካዊ ፍቅሩ እኩል ይወዳል፤ ነገር ግን በልጆቹ ሁሉ እኩል

ደስ ይለዋል ማለት አይደለም፡፡ እንደ አብርሃም በተስፋው ቃል በማይጠራጠሩ ደስ ይሰኛል፡፡

2. ያለ እምነት ዓለምን ማሸነፍ አይቻልም፡፡

«ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና፤ ዓለምን የሚያሸንፈው እምነታችን ነው፡፡» (1ዮሐ. 5÷4)

3. እምነት ጋሻችን ነው፡፡

ያለ እምነት የጠላትን ውጊያ (ክስ፣ ሽንገላ) መቋቋምና መቃወም አንችልም፡፡

«... የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፡፡» (ኤፌ. 6÷16)

«በመጠን ኑሩ ንቁም፤ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና፤ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት፡፡» (1ጴጥ. 5÷8-9)

4. በመንፈሳዊ ሕይወታችን ጸንተን የምንቆመው በእምነታችን ነው፡፡ (2ቆሮ. 1÷24)

5. ጻድቅ የሚኖረው በእምነቱ ነው፡፡ (ዕን. 2÷4፤ ዕብ. 10÷38፤ ሮሜ 1÷17፤ ገላ. 3÷11)

6. የምናደርገውን ሁሉ በእምነት ማድረግ አለብን
«ከእምነት ያልሆነ ሁሉ ኀጢአት ነው፡፡» (ሮሜ 14÷23)

7. እምነት ከእግዚአብሔር የምንቀበልበት እጅ ነው፡፡
«እምነትሽ አድኖሻል፤» «እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ» (ማቴ. 9÷22፡29)
«ለሚያምን ሁሉ ይቻላል፡፡» ማር. 9÷23

8. ያለ እምነት የምንጸልየው ጸሎት አይመለስም፡፡

«ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፡፡ የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና፤ ሁለት ሐሳብ ላለው፣ በመንገዱም ለሚወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው፡፡» (ያዕ. 1÷6-8)

«ስለዚህ እላችኋለሁ የጸለያችሁትን፣ የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁ እመኑ፤ ይሆንላችሁማል፡፡» (ማር. 11÷24)





## ፫. የእምነት ደረጃዎች

እግዚአብሔርን ማመን የተለያዩ ደረጃዎች አሉት፡-

1. የማያድን እምነት አለ፡፡

የእግዚአብሔርን መኖር ማመን ብቻ አያድንም፡፡
«እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ፤ ይንቀጠቀጡማል፡፡» (ያዕ. 2÷19)

2. ደኅንነትን (የዘላለም ሕይወትን) ያገኘንበት እምነት አለ፡፡
«ጸጋው በእምነት አድኖአችኋል፡፡» (ኤፌ. 2÷8)

«ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤» (ሮሜ 10÷9) ደኅንነት ያገኘንበትን እምነት የሰጠን እግዚአብሔር ራሱ ነው፡፡ የወንጌልን ቃል ሰምተን ልባችንን ወደ እግዚአብሔር እንዲያዘነብል በምናደርግበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር የእምነት ዘር ለእያንዳንዳችን ይሰጣል፡፡

«እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንዳካፈለው፣ እንደ ባለአእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው ዐልፎ በትዕቢት እንዳያስብ፡፡» (ሮሜ 12÷3)
እግዚአብሔር በልባችን የዘራው ይህ የእምነት ዘር መኰትኰትና ማደግ አለበት፡፡

3. ትንሽ (ጐደሎ) እምነት አለ፡፡

«እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን፣ ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን የሜዳን ሣር እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ፣ እናንተ እምነት የጐደላችሁ እናንተንማ ይልቁን እንዴት?» (ማቴ. 6÷30)

«እናንተ እምነት የጐደላችሁ ለምን ትፈራላችሁ? (ማቴ. 8÷26)
«እንዲህ የምትፈሩ ለምንድን ነው? እንዴት እምነት የላችሁም?» (ማር. 4÷40)

«ወዲያውም ኢየሱስ እጁን ዘርግቶ ያዘውና (ጴጥሮስን) አንተ እምነት የጐደለህ ስለ ምን ተጠራጠርህ? አለው፡፡» (ማቴ. 14÷31)

4. ትልቅ እምነት

«በዚያን ጊዜ ኢየሱስ መልሶ፣ አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው፤ እንደ ወደድሽ ይሁንልሽ አላት፡፡» (ማቴ. 15÷28)

«ኢየሱስም ሰምቶ ተደነቀና ለተከተሉት እንዲህ አለ፤ እውነት እላችኋለሁ በእስራኤል እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም፡፡» (ማቴ. 8÷10)

ከላይ እንዳነበብነው ኢየሱስ በዚያ ሰው ትልቅ እምነት ተደነቀ፡፡ በሌላ ቦታ ደግሞ ኢየሱስ በሰዎች አለማመን እንደ ተደነቀ እናነባለን፡፡

«ስለ አለማመናቸውም ተደነቀ፡፡» (ማር. 6÷6)

በእኛስ ሕይወት? ኢየሱስ የሚደነቀው በእምነታችን ትልቅነት ነው ወይስ በአለማመናችን ትልቅነት?

### 5. ግብዝነት የሌለበት እምነት

«የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልብና ከበጎ ኅሊና፣ <u>ግብዝነትም ከሌለበት እምነት</u> የሚወጣ ፍቅር ነው፡፡» (1ጢሞ. 1÷5)
ይህ የእምነትን <u>ጥራት</u> ያመለክታል፡፡

በመጀመሪያ ማተኮር ያለብን በእምነታችን ጥራት ላይ ነው እንጂ ጥንካሬው ላይ አይደለም፡፡ ግብዝነት ያለበት ትልቅ እምነት ከሚኖረን የነጠረች ንጽሕት ትንሽ እምነት ብትኖረን ይሻላል፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ንጹሕና ትልቅ እምነት ያለው ሰው እግዚአብሔርን የበለጠ ደስ ያሰኛል፡፡

እምነታችን የሚነጻው በፍቅር ሲታቀፍ ነው፡፡ «በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ <u>በፍቅር የሚሠራ እምነት</u> እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና፡፡» (ገላ. 5÷6)

## ፬. <u>እምነት ከየት ይመጣል?</u>

እምነት የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡
«እምነት ከመስማት ነው፤ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡» (ሮሜ 10÷17)

መጥምቁ ዮሐንስ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ «የዓለምን ኀጢአት ሁሉ የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ነው» ብሎ በዮሐ. 1÷29 ከመሰከረ በኋላ እስር ቤት ገብቶ በመከራ ውስጥ ሲያልፍ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊመጣ ያለው መሲሕ መሆኑን እንኳ መጠራጠር ጀምሮ ነበር፡፡ በማቴ. 11÷2-6 ላይ «የሚመጣው አንተ ነህን ወይስ ሌላ እንጠብቅ?» ብሎ ወደ ኢየሱስ መልእክተኞች መላኩን እናነባለን፡፡ ኢየሱስ ግን የሰጠው መልስ፤ «ነኝ» ወይም «አይደለሁም» የሚል ሳይሆን «ሄዳችሁ ያያችሁትን፣ የሰማችሁትንም ለዮሐንስ <u>አውሩለት፤</u> ዕውሮች ያያሉ፤ ዐንካሶችም ይሄዳሉ፤ ለምጻሞች ይነጻሉ፤ ደንቈሮዎችም ይሰማሉ፤ ሙታንም ይነሣሉ፤ ለድኾችም ወንጌል ይሰበካል፤ በእኔም የማይሰናከለው ብፁዕ ነው፡፡» የሚል መልስ ነበረ፡፡ እምነቱ እንደ ደከመ አይቶ <u>እምነቱን የሚያነቃቃ ቃል</u> ነበረ የላከለት፡፡ እምነት የሚመጣው የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት ነውና፡፡





በእኛም ሕይወት ደኅንነትን ያገኘንበት እምነት ወደ ልባችን የመጣው የወንጌልን ቃል ከሰማን በኋላ ነው፡፡ «ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም በሕያውና ለዘላለም በሚኖር <u>በእግዚአብሔር ቃል</u> ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ፡፡» (1ጴጥ. 1÷23)

## ፭. <u>እምነታችን እንዴት ያድጋል?</u>

### 1. ቃሉን <u>አድራጊዎች</u> በመሆን

«ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ፡፡» (ያዕ. 1÷22)

ብረት የሚያነሡ ሰዎች ጡንቻቸው እየጠነከረ እንደሚሄድ ሁሉ እኛም መንፈሳዊ ጡንቻችን (እምነታችን) እያደገ የሚሄደው እምነታችንን ሥራ ላይ ስናውለው ነው፡፡ አምናለሁ የምንለውን የእግዚአብሔርን ቃል በተግባር ስንገልጸውና ስንኖረው ማለት ነው፡፡

### 2. የእግዚአብሔርን ቃል በተመገብነው መጠን

ሰውነታችን ለማደግ ሥጋዊ ምግብ እንደሚያስፈልገው ሁሉ፣ መንፈሳዊ ሕይወታችንም (እምነታችን) ለማደግ የቃሉ ወተትና ሥጋ ያስፈልገዋል (1ጴጥ. 2÷1-2፤ 1ቆሮ. 3÷1-2)፡፡

«እምነት በውስጣችን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመወለድ የእግዚአብሔር ቃል እንዳስፈለገው ሁሉ፣ ለማደግም የእግዚአብሔር ቃል ያስፈልገዋል (ሮሜ 10÷17)፡፡

### 3. በበጎ ኅሊና

«እምነትና <u>በጎ ኅሊና ይኑርህ</u>፤ አንዳንዶች ኅሊናን ጥለው መርከብ አለ መሪ እንደሚጠፋ በእምነት ነገር ጠፍተዋልና፡፡» (1ጢሞ. 1÷19)

በጎ ኅሊና ስንል የማይከሰንና ያልጐደፈ ኅሊና ማለታችን ነው፡፡ በእግዚአብሔርም ሆነ በማንኛውም ሰው ፊት ስንቆም ኅሊናችን ስለ ምንም ነገር የማይወቅሠን ከሆነ፣ በጎ ኅሊና አለን ማለት ነው፡፡ ጳውሎስ በሐዋ. 24÷16፣ «ስለዚህ እኔ ደግሞ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ሁልጊዜ <u>ነውር የሌለባት ኅሊና</u> ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ፡፡» የሚለው ለዚህ ነው፡፡

በጎ (ንጹሕ) ኅሊና ከሌለን ሕያው እግዚአብሔርን ማምለክ አንችልም፡፡ መፍትሔው የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ደም ነው፡፡ «ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ኅሊናችሁን ያነጻ ይሆን?» (ዕብ. 9÷14)

«የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ (ኀሊናችንን) ያነጻናል።» (1ዮሐ. 1÷7)

በጎ ኀሊና የእምነት መሪና ጠባቂ ነው። በጎ ኀሊና ከሌለን እምነታችን እየደፈረሰ ይሄዳል።

## ፯. እምነት እንዴት ይገለጣል?

«ወንድሞቼ ሆይ፤ እምነት አለኝ የሚል ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን? ... ሥራ የሌለው (በተግባር የማይገለጥ) እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው። ... ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።» (ያዕ. 2÷14-26 በሙሉ ያንብቡ)

እውነተኛ እምነት በተግባር የሚገለጥ እምነት ነው። በአፉ ብቻ እምነት አለኝ የሚል ሰው በተግባር ግን ለሰዎችም ሆነ ለእግዚአብሔር የሚታይ ሥራ ከሌለው፣ እምነቱ የአፍ እምነት ብቻ ነው። አንድ ሰው ምንም ገንዘብ ሳይኖረው በአፉ ሀብታም ነኝ እያለ ቢያውጅ ሀብታም እንደማይሆን ሁሉ፣ አንድ ሰው እምነት አለኝ ስላለ ብቻ እምነት አለው ማለት አይደለም። በተግባር የማይገለጥ እምነት የሞተ ነውና።

ለምሳሌ፦ አንድ ሰው፣ «የሚጠብቅህ አይተኛም፤ አያንቀላፋምም» የሚለውን የእግዚአብሔርን የጥበቃ ቃል አምናለሁ እያለ ሌሊቱን ግን ተጨንቆ የሚያድር ከሆነ፣ እምነቱ እውነተኛ እምነት አይደለም። እምነቱን በተግባር አልገለጸም። «የሰማይ አዕዋፍን የሚመግብ አምላክ እናንተንም ይመግባል።» የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል አምናለሁ እያለ የዕለት እንጀራዬን ከየት አገኝ ይሆን? ብሎ የሚጨነቅም ሰው እምነቱን በተግባር አልገለጸም።

## ፰. የእምነት ጠላቶች

### 1. ፍርሀት

ፍርሀትና እምነት እንደ ብርሃንና ጨለማ ናቸው። አንዱ ያለበት ሌላው ሊኖር አይችልም። ጤናማ የሆነ፣ ሊኖረን የሚገባን ዐይነት ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍርሀት አለ። ይህ ዐይነቱ ጤናማ ፍርሀት ከክፉ ነገር፣ ከዐጉል ድፍረትና ከትዕቢት የሚጠብቀን ፍርሀት ነው። «ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ» (ሮሜ 11÷20)

የእምነት ጠላት የሆነው ፍርሀት ግን ከእግዚአብሔር ሳይሆን፣ ከጠላታችን ከዲያብሎስ የሚመጣ ነው። «እግዚአብሔር የኀይልና የፍቅር፣ ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሀት መንፈስ አልሰጠንምና።» (2ጢሞ. 1÷7) ይህ ዐይነቱ ፍርሀት በሕይወታችን እስራትን ያመጣል። «ሰውን መፍራት ወጥመድ ያመጣል፤ በእግዚአብሔር የሚታመን ግን እርሱ ይጠበቃል።» (ምሳሌ 29÷25)



የክርስትና መሠረት ትምህርት - ክፍል ፩

እምነት የሚመጣው የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት የሆነውን ያህል፣ ፍርሀት ደግሞ የሚመጣው የሰይጣንን ቃል (ሐሳብ) በመስማት ነው። ጆሮአችንን ለሰይጣን በሰጠን መጠን ደግሞ በፍርሀት እንሞላለን። ጆሮአችንን ለእግዚአብሔር ቃል በሰጠን መጠን በእምነት እንሞላለን። በማር. 5÷21-43 (ክፍሉን በሙሉ ያንብቡ) ላይ ልጁ በሞት አፋፍ ላይ ሆኖ ኢየሱስ እንዲፈውስለት ወደ ኢየሱስ መጥቶ የነበረው የኢያኢሮስ ታሪክ ይህን ያሳየናል። ሰዎች መጥተው «ልጅህ ሞታለች ስለ ምን መምህሩን አሁን ታደክመዋለህ?» (ቍ 35) ብለው መርዶ ባመጡለት ጊዜ፣ ኢየሱስ የኢያኢሮስ እምነት በፍርሀት ሊሸነፍ መሆኑን አይቶ «<u>እመን ብቻ እንጂ አትፍራ» (ቍ 36</u>) ብሎ እምነቱን ሲያበረታታለት እናነባለን። በእኛም ሕይወት አንዳንድ ጊዜ ዲያብሎስ ልዩ ልዩ ዐይነት የፍርሀት መርዶ እያመጣ እምነታችንን ሊያዳክም ይሞክራል። የዲያብሎስን መርዶ ከሰማን በፍርሀት እንሸነፋለን። መስማት ያለብን «እመን ብቻ እንጂ አትፍራ» የሚለውን የጌታን ቃል ነው።

መፍራት የሌለብን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለ ሆነ ነው። «አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም።» (መዝ. 23÷4)

«በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና፤ አይዞህ አትፍራ፤ አትደንግጥ።» (ኢያሱ. 1÷9)
«አብራም ሆይ፣ አትፍራ፤ እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ።» (ዘፍ. 15÷1)

### 2. ጥርጥር

ሌላው የእምነት ጠላት ጥርጥር ነው። ጥርጥር ማለት በአንድ ነገር ላይ ልባችን (ሐሳባችን) ለሁለት ሲከፈል ነው። መጠራጠር ማለት በሁለት ሐሳብ መዋለል ማለት ነው።

ጥርጥር በሕይወታችን እያለ እምነታችን ሊሠራ አይችልም።

«ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና። ሁለት አሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው።» (ያዕ. 1÷6-8)

ጴጥሮስ በእምነት በውሃ ላይ መራመድ ከጀመረ በኋላ በልቡ ጥርጥር ሲፈጠር መስጠም ጀመረ፤ «ሊሰጥምም በጀመረ ጊዜ፣ ጌታ ሆይ አድነኝ ብሎ ጮኸ። ወዲያውም ኢየሱስ እጁን ዘርግቶ ያዘውና <u>አንተ እምነት የጎደለህ ስለ ምን ተጠራጠርህ</u>? አለው።» (ማቴ. 14÷30-31) ጥርጥር ያሰጥመናል፤ እምነት ያንሳፍፈናል።

«(አብርሃም) በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት <u>በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም።</u>» (ሮሜ 4÷21)

### 3. አለማመን

አለማመን በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ቃል ላይ ከመታመን ይልቅ በዐምስቱ የስሜት አውታሮቻችን (ማየት፣ መስማት፣ ማሽተት፣ መዳሰስና መቅመስ) መተማመን ማለት ነው፡፡

«እርሱ ግን (ቶማስ)፡ - የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ፣ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ፣ እጄንም በጐኑ ካላገባሁ አላምንም አላቸው፡፡» (ዮሐ. 20÷25) ቶማስ የበለጠ የተማመነው በማየትና በመዳሰስ የስሜት አውታሮቹ እንጂ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት፣ «የሰው ልጅ ከሙታን ይነሣል» ብሎ ስለ ራሱ በተናገረው ቃል አልነበረም፡፡

በኋላም ኢየሱስ፣ በዮሐ. 20÷27-29፣ «ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን፤ ... ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው» ሲለው እናነባለን፡፡

አለማመናችን በግል ሕይወታችንም ሆነ በመካከላችን ጌታን እንዳይሠራ ያደርገዋል፡፡ «በአለማመናቸውም ምክንያት በዚያ ብዙ ተኣምራት አላደረገም፡፡» (ማቴ. 13÷58)

በአለማመናችን ምክንያት እግዚአብሔር ወዳዘጋጀልን ዕረፍት መግባት ይሳነናል፡፡ «ካልታዘዙትም በስተቀር ወደ ዕረፍቱ እንዳይገቡ የማለባቸው እነማን ነበሩ? ባለማመናቸውም ጠንቅ ሊገቡ እንዳልተቻላቸው እናያለን፡፡» (ዕብ. 3÷18-19)

ተስፋ፣ እግዚአብሔር የገባልኝ የተስፋ ቃል ይሆናል ይላል፡፡

እምነት፣ እግዚአብሔር የገባልኝን የተስፋ ቃል እንደ ሆነ አድርጌ እቀበለዋለሁ ይላል፡፡

ጥርጥር፣ ይሆናል ወይስ አይሆንም በማለት በእምነትና በአለማመን መካከል ይዋዥቃል፡፡

አለማመን፣ እንዴት ተደርጎ! በጭራሽ ሊሆን አይችልም ይላል፡፡

### 4. ኀጢአት

ኀጢአት በልባችን እያለ የእምነትን ጸሎት መጸለይ አንችልም፡፡ «በልቤስ በደልን አይቼ ቢሆን ጌታ አይሰማኝም ነበር፡፡» (መዝ. 65(66)÷18)

«እነሆ፣ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም፤ ጆሮውም ከመስማት አልደነቈረችም፤ ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፣ እንዳይሰማም ኀጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል፡፡» (ኢሳ. 59÷1-2)





ኀጢአት በልባችን እያለ የእምነትን ውጊያ መዋጋት አንችልም፡፡ «ጠላቶችህን ልትወጋ በወጣህ ጊዜ ከክፉ ነገር ሁሉ ሰውነትህን ጠብቅ፡፡» (ዘዳ. 23÷9)

«... እስራኤል በድሏል፤ ... ስለዚህም የእስራኤል ልጆች በጠላቶቻቸው ፊት መቆም አይችሉም፡፡» (ኢያሱ 7÷11-12)

ኀጢአት እምነታችንን አሰናክሎብን ከሆነ መፍትሔው በንስሓ ወደ ጌታ ቀርበን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአታችን መንጻት ነው፡፡ «የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል፡፡ ኀጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም፡፡ በኀጢአታችን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዐመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው፡፡» (1ዮሐ. 1÷7-9)

### 5. አለማወቅ

ሌላው የእምነት ጠላት አለማወቅ ነው፡፡

«ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል፡፡» (ሆሴ. 4÷6)

በዚህ ጥቅስ ውስጥ የተገለጸው ዕውቀት የሚያመለክተው፣ ትምህርት ቤት ሄደን የምናገኘውን ዕውቀት ሳይሆን እግዚአብሔርንና ቃሉን ማወቅን ነው፡፡

ሰዎች ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔርን ነገር የሚስቱት የእግዚአብሔርን ቃል ካለማወቅ እንደ ሆነ ኢየሱስ ተናግሮአል፤ «ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኀይል አታውቁምና ትስታላችሁ፡፡» (ማቴ. 22÷29)

ለዚህ ነው እግዚአብሔር በሆሴዕ 6÷6፣ «ከመሥዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ እወዳለሁ፡፡» ያለው፡፡

«ዕረፉ እኔም አምላክ (የሁሉ ገዥ) እንደ ሆንሁ ዕወቁ፡፡» (መዝ. 64÷10)

«አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ይበረታሉ፤ ያደርጋሉም፡፡» (ዳን. 11÷32)

«ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ የእግዚአብሔርን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም፡፡» (1ቆሮ. 2÷12)

«ስለ መንፈሳዊ ነገርም ወንድሞች ሆይ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ፡፡» (1ቆሮ. 12÷1)

በክርስቶስ ያለውን ማንነቱን የማያውቅ ክርስቲያን ጠላት ሲጫወትበት ይኖራል፡፡ ለዚህ ነው ጳውሎስ በኤፌ. 1÷17-18 እንዲህ ብሎ ለኤፌሶን ሰዎች የሚጸልየው፤ «የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ

እለምናለሁ። ይህም የልባችሁ ዐይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንደ ሆነ፣ በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የክብር ባለጠግነት ምን እንደ ሆነ ለምናምንም ከሁሉ የሚበልጥ የኀይሉ ታላቅነት ምን እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ ነው።» ሐዋርያው በዐጭሩ ክርስቶስንና በክርስቶስ ማን መሆናችሁን ታውቁ ዘንድ እጸልይላችኋለሁ ማለቱ ነው።

**እግዚአብሔር እርሱን ደስ የምናሰኝ የእምነት ሰዎች ያድርገን!**





## ትምህርት አራት፡- እምነት

የመታወቂያ ቁጥር፤ ____________________

ስም፤ ____________________

አድራሻ፤ ____________________

____________________

____________________

1. ዕብራውያን ምዕራፍ 11 የእምነት ምዕራፍ ተብሎ ይጠራል። በቍጥር 1 ላይ ስለ እምነት የተጻፈውን እንዴት ትረዳዋለህ?

2. እምነት በክርስቲያን ሕይወት ያለውን አስፈላጊነት አስረዳ።

3. ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ጢሞ. 1÷5 እና በ2ጢሞ. 1÷5 «ግብዝነት የሌለበት እምነት» ሲል ምን ማለቱ ነው?

4. በጥናቱ እንደ ተገለጸው የእምነት ደረጃዎች ተብለው ከተጠቀሱት ውስጥ አንተን የሚመለከት የትኛው ደረጃ ነው? ካለህበት ደረጃስ ከፍ ለማለት መውሰድ ያለብህ ርምጃ ምንድን ነው?

5. «እምነት ያለ ሥራ የሞተ ነው» ሲል ምን ማለቱ ነው?

6. እምነት እንዲያድግ ምን ምን ማድረግ ያስፈልጋል?

7. ለእምነት ዕንቅፋት የሆኑትን ነገሮች ከዘረዘርህ በኋላ ከእነዚህ ዕንቅፋቶች ውስጥ ለአንተ እምነት ዕንቅፋት ሆኖብህ የሚያውቀውን አንዱን አብራራ። ይህንን ዕንቅፋት ከሕይወትህ ለማስወገድ የወሰድኸው ወይም መውሰድ ያለብህ ርምጃ ምንድን ነው?